**ዮም ፍሥሓ ኮነ!**
**በእንተ በዓለ ስደቶሙ፡**
**ለሕፃን ኢየሱስ መሚሕ፥ ወለእሙ ድንግል ማርያም!**

**+ + +**

# ከኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት።

## ለክቡራንና ለክቡራት አንባቢዎቻችን፡-

በቀደሙትና በዘንድሮው፡ የ፳፻፰ ዓመተ ምሕረት፡ የታላቁ የአዲስ ዘመን የዐውደ ዓመት በዓል መልእክታችን ውስጥ፡ **"ወርኀ-ጽጌ"** በሚለው ዋና ርእስ፥ ከዚያም፡ **"ጾመ ስደትና ማኅሌተ-ጽጌ"** በሚለው ንኡስ አርእስት ሥር፡ *«"የጾመ-ስደት" እና "የወርኀ-ጽጌ" ምሥጢር፡ ኢትዮጵያዊው ሊቅ፡ ገዳማዊ ጊዮርጊስ፡ ዘሀገረ-ጋሥጫ፡ "ሰቆቃወ-ድንግል" እና "ማኅሌተ-ጽጌ" በተባሉት፡ በግእዙ፡ የመልክዓታት ድርሰቶቹ፡ ገላልጦ፡ በሰፊው ተናግሮታል።"* በሚለው ዓቢይ ዐረፍተ-ነገር መግቢያ ላይ፡ *"ገዳማዊ ጊዮርጊስ፡ ዘሀገረ-ጋሥጫ፡"* የሚለው የስም ሓረግ፡ **"ገዳማዊ ጽጌ ድንግል"** ተብሎ ይነበብ ዘንድ፡ የተስተካከለ መኾኑን ስናሳውቃችሁ፡ ለደረሰው ስሕተት፡ ይቅርታችሁን እየጠየቅን ነው።

---